

# ንገሯት!

ሁላችሁ እናንት የሰው ልጆች
አስረዷት፣
በሉ, ቁሙ፣ ሃይል ያላችሁ፤
ተማርን፣ ሰልጥነናል፣አውቀናል፣ ያላችሁ።
በሉ ተነሱ በቋንቋ ከሆነ ሚዛኑ

## ንገሯት!

በሉ ተናገሩ፣
የትግሬ፣ የጉራጌ፣የአደሬ፣
የኦሮሞ ...ወዘተ ልጆች
በክልል የምታምኑ፤
ቁሙ ተፋረዱ

## ንገሯት!

ለዚያች ዓማርኛ ለምትናገር እናት፤
አስረዷት ቋንቋ መሆኑን ሚዛኑ
ለፍርድም ሆነ ለመኖር በህይወት፤
በሉ በጥቅሻ አሳምኗት፣
ያችን ዓማርኛ የምትናገር እናት፤።
በተማራችሁት፣
በምታስተምሩበት፤
ቋንቋ ከሆነ ሚዛኑ
ሰው የሚለካበት፣
በሉ እናተው አስተምሯት፤
ያችን ያማራ እናት።

## ንገሯት!

በጥቅሻ አስረዷት፣
ከእንግዲህ ልጅ የሚሉት፤
እንዳትወልድ በኢትዮጵያ አህጉራት።

## ለዓለም በማወጅ ንገሯት!

በሉ እንጅ የስልጣኔውን መንገድ አሳይዋት፣
ያችን ዛሪ ጎጤ ሳትል፤
ሳይገባት የወለደችውን በክልል።

ሚዛን ከሆነ ቋንቋ፤
በመጮህ ወይም በጥቅሻ፣
አስታውቋት እንጅ
ጅብ እንዳዬ ውሻ።
ሚዛን ከሆነ ቋንቋ፤
ትባረር ወይስ ተዘፈቃ ትሙት
በክልል አረንቋ?
ትፈንገል ብላችሁ ከፈረዳችሁ
ሰው መሆኗ እንዲፋቅ በዚያ ቦታ፤
የሐጤአቷን ሃቅ እኔ ልመስክርላት፣
መሆኑን ላስረዳ
ተሸካሚነቷንም ላሳይ
ልክ እንደ ተባለው ሁሉ፣
“አይጥ በበላ ያው ዳዋ ተመታ”!



# ንገሯት!

**© ለምለም ፀጋው ፤ ሚያዝያ 8፣2005 ሁናቴውን አዳምጡ!**
http://www.zegabi.com/v/watch.php?vid=3c0f18fef

*Lemlem Tsegaw,* April 16, 2013